# እምቢ በል አማራ!




እንደ አርበኛ አያትህ እምቢ በል አማራ፣
ለጂላንፎች አትሁን ቁማር መጫወቻ!

እንደ በጎች አርደው እንደ አውሬ ዘንችረው፣
ለበሉት ወገንህ አለሁ እንዳትለው፣
ድምጥህንም ዘጉት ጉረሮህን አንቀው፡፡

ተእነሱ ተባብረው ምሁር ነን የሚሉት፣
ወንጀል ሊሸፍኑ ጀመሩ ዓባይ ስብከት፣
ደምህ ግምጃ ሆኖ ኢትዮጵያን ሲያለብሳት፡፡

ጨካኝ ተማርን ባዮች ለነፍስ የማያዝኑ፣
የአማራን ዘር ፍጅት ጀሮ ዳባ እያሉ፣
ግድብ ትራንፕ ብለው ያረጠርጣሉ፡፡

እምቢ በል አማራ እያዘናጉህ ነው፣
ደምህን ረግጠው ውሀ ሊቀዱ ነው፡፡

አለዚያማ ለዓባይ ተአንተ ቀርበውት ነው፣
ባሳረዱህ ቁጥር ግድብ ስብከታቸው?

በመላ አገሪቱ አጥንትህን ቆርጥመው፣
ተዓባይ ውሀ ቀድተው ሊያወራርዱት ነው፣
ዘራፍ በል አማራ ጨፍጫፊህ አውሬ ነው፡፡

ለዓመታት ለወራት በዓይንህ እንዳየኸው፣
የኢትዮጵያ ሱሴ እቅድና አላማው፣
አንተን አደንዝዞ ደምህን መምጠጥ ነው፡፡

ስንሞት ኢትዮጵያ እያሉ የዋሹህ፣
በስብከት መጫኛ ጠልፈው እየጣሉህ፣
በካራ እያረዱ ቀርጥፈው ሊበሉህ፡፡

ድፍን አማራ ሆይ ልቡናህን አንቃው፣
እንደ ቅድመ አያትህ ቆቅን ሁንባቸው፣
ምላስ መስማት ትተህ ልባቸውን እየው፡፡

እናት ኢትዮጵያን እንጀራቸው አርገው፣
አንተን ልጇን ደሞ የዶሮ ወጥ ሰርተው፣
እንደ ጆፌ አሞራ ጥርግ አርገው በልተው፣
እርሷንም አንተንም ታሪክ ሊያደርጉ ነው፡፡

ለግማሽ ምእተ ዓመት ሲያድሙ የኖሩ፣
አማራን ቆራርጠው ቅቅል እየሰሩ፣

**ኢትዮጵያን ቀዳደው እየፈተፈቱ፣**
**ስልቅጥ አርገው በልተው ተካርታ ሊያጠፉ፡፡**

**ልክ እንደ አያቶችህ ጎራው በል አማራ፣**
**እንደ ቅድመ አያትህ ሞረሽ ተጠራራ፣**
**ተኢትዮጵያ አውሮጳ ተአውሮጳ አሜሪካ፣**
**ተሜልቦርን ኤስያ ተኤስያ አፍሪካ፣**
**እንደ አንበሳ አግስተህ እምቢ በል አማራ!**

**በላይነህ አባተ** (abatebelai@yahoo.com)
**ጥቅምት ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.**